**Hallo**
**Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ት/ቤት እና ትምህርት

የትምህርት ስርዓት
የግዴታ ት/ቤት
የሙያ ትምህርት / መካከለኛ ትምህርት ቤት
ዩንቨርስቲ / ተግባራዊ የሳይንስ ዩንቨርስቲ
የዲፕሎማ ዕውቅና

# የትምህርት ስርዓት

ስዊዘርላንድ ውስጥ መማናቸውም ግዜ ትምህርት መማር እና በግል ዕውቀትን ማዳበር ይቻላል። በተለይ የሙያ ስልጠና ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው። የሙያ ስልጠና የሚያደርግ ሰው፣ ስልጠናውን ሲጨርስ ሌላ ቀጣይ ስልጠና ወይም ዩንቨርስቲ መቀጠል ይችላል።

## ተከታታይ ትምህርት / ኃላፊነቶች

ስዊዘርላንድ ውስጥ ተከታታይ የሆኑ ሶስት የትምህርት ደረጃዎች አሉ።

- የግዴታ ትምህርት ቤት (Volksschule: Kindergarten, Primarschule und Sekundarstufe I)
- መሰረታዊ የሙያ ትምህርት ወይም መካከለኛ ትምህርት (Sekundarstufe II)
- ከፍተኛ የሙያ ዩንቨርስቲ / መደበኛ ዩንቨርስቲዎች እና ከፍተኛ የሙያ ትምህርት ቤቶች (Tertiärstufe)

መንግስታዊ /ህዝባዊ/ ማዕከላት ለሙያ ትምህርት በበላይነት ይቆጣጠራሉ። በፌደሬሽን፣ በካንቶን እና በኮምዩኖች ደረጃ ተግባርና ሃላፊነቱን ይጋራሉ። በየካንቶኖቹ የተለያየ ዓይነት ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ስርዓቶች ያሉት በዚህ ምክንያት ነው።

## የመማር ግዴታ

በ Basel-Stadt ካንቶን የግዴታ ትምህርት 11 ዓመት ይወስዳል። ይህም ማለት፣ ተማሪዎች የግድ 11 ዓመት መማር አለባቸው። ልጅ ትምህርት የሚጀምረው 1 ዓመት ዕድሜ ሲሞላው ነው። ልጅዎ ትምህርት ቤት መሄድ ካልቻለ፣ ለልጅዎ ት/ቤት ይቅርታ መጠየቅ አለብዎት። ልጆች ይቅርታ ሳይጠቁ ከትምህርት ቤት ቢቀሩ፣ ወላጆች ሊቀጡ ይችላሉ።
ልጆች ዕድሚያቸው 16 ዓመት ከመሙላታቸው በፊት ወደ ባዝል ከተማ አዲስ ከመጡ፣ የግዴታ ትምህርት ቤት መማር ይፈቀላቸዋል። ነገር ግን ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በላይ የሆኑ ወጣቶች ወደ ባዝል ከተማ አዲስ ከመጡ፣ የሙያ ትምህርት መረጃ ማዕከል (Berufsinformationszentrum, BIZ) መማር ይችላሉ።. የሙያ ትምህርት መረጃ ማዕከሉ (BIZ) ወጣቶች የትኛውን ዓይነት ትምህርት እና የሙያ ስልጠና ማድረግ እንደሚችሉ መረጃዎችን ይሰጣል።

## ከግዴታዊ ትምህርት በኋላ የሙያ ስልጠና

ወጣቶች ከግዴታዊ ትምህርት በኋላ የሙያ ስልጠና ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ወጣቶች መሰረታዊ የሙያ ስልጠናን ይመርጣሉ። (የሙያ ትምህርት፣ Berufslehre). ከጊዜ በኋላ ቆይተው ከፍተኛ የሙያ ስልጠና ትምህርት (höhere Berufsbildung) ያደርጋሉ። ይህንን ስልጠና እየወሰዱ በጎን ወይም ከስልጠናው በኋላ የሙያ ባካሎሬት (Berufsmaturität) መውሰድ ይችላሉ። ከዚህ ትምህርት በኋላ ተግባራዊ የሳይንስ ዩንቨርስቲ (Fachhochschule) መቀጠል ይችላሉ። በግምት 20 በመቶ የሚሆኑት ወጣቶች በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቀው (የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ባካሎሬት፣ gymnasiale Maturität) ይወስዳሉ። ከማትሪክ ውጤት በኋላ መደበኛ ዩንቨርስቲ መግባት ይችላሉ።

## ስኮላርሺፕ

በቂ ገንዘብ ለሌላቸው ሰዎች ቀጣይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመማር እና የሙያ ስልጠና ትምህርት ለማድረግ ስኮላርሺፕ (Stipendien) ይሰጣል። እነዚህ ተማሪዎች ከግዴታው ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ለሙያ ስልጠና ትምህርት ገንዘብ ይሰጣቸዋል። ከሌላ ክልል የእና የመጡም ቢሆኑና Basel-Stadt ግን የሚኖሩ ከሆነ ስኮላርሺፕ ሊሰጣቸው ይችላል። ወሳኙ ግን ከየት አገር እንደመጡ እና ምን ያህል ግዜ ስዊዘርላንድ እንደኖሩ ነው። የካንቶን አስተዳደር ጽ/ቤት ከሙያ ስልጠና ስኮላርሺፕ ሰጪ ቢሮ (Amt für Ausbildungsbeiträge) ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/schule-und-bildung/bildungssystem

# የግዴታ ት/ቤት

**በግዴታ ትምህርት ቤት ውስጥ ልጆች መሠረታዊ ትምህርት ይቀበላሉ።. ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ስልጠና ሊያደርጉ ይችላሉ።.የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ነፃ ናቸው።**

## ልጅን ማስመዝገብ

የሕዝብ /የመንግስት/ ትምህርት ቤቶችን የማስተዳደር ኃላፊነት ያላቸው የኮምዩን ማዘጋጃ ቤቶች ወይም ካንቶኖች ናቸው።
ልጅዎን እዚህ ያስመዝግቡት፡-
*መዋዕለ ሕፃናት ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዝገባ፣*

- በባዝል-ከተማ ላሉ ልጆች፡ ባዝል-ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
- በሪሄን ላሉ ልጆች፡ የሪሄን የኮሚዩን ትምህርት ቤት
- በቤቲንገን ላሉ ልጆች፡ የማህበረሰብ ትምህርት ቤት ቤቲንገን።

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዝገባ፣

- ባዝል-ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

## የትምህርት ቤት ደረጃዎች

የግዴታ ትምህርት ቤት 3 ደረጃዎች አሉት። ደረጃዎቹም ተከታታይ ናቸው።

- መዋዕለ ሕፃናት (Kindergarten) ለ2 ዓመታት ይፈጃል፣.
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (Primarschule) ለ6 ዓመታት ይቆያል።. ልጅዎ ልዩ ድጋፍ ያስፈልገዋል ወይንስ ልዩ ችሎታዎች አሉት? ይህም ከሆነ እዚህ ትክክለኛውን ድጋፍ ያገኛል።
- የላይኛው ደረጃ ትምህርት (Sekundarstufe I) ለ3 ዓመታት ይቆያል።. በላይኛው ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሦስት የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች አሉ (A-Zug, E-Zug, P-Zug). የትምህርት ቤቶች ዓይነቶች የተለያየ ክብደት አላቸው።
- ጀርመንኛ የልጅዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ አይደለም? ከዚያም በሶስቱም ደረጃዎች ላይ ልዩ ድጋፍ ያገኛል።

## ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ- እና በራስ ባህል መማር (HSK)

ከግዳጅ ትምህርት በተጓዳኝ ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እና ባህላቸው (heimatliche Sprache und Kultur, HSK) ኮርሶች መከታተል ይችላሉ። ልጆቹ ቋንቋውን ይማራሉ እና በተሻለ ሁኔታ መረዳት፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ይማራሉ።. እና ስለትውልድ አገራቸው ታሪክ ፣ ጂኦግራፊ ፣ በዓላት እና ወጎች ያውቃሉ። እነዚህን ኮርሶች እንዲማሩ እንመክራለን።. በፈቃደኝነት የሚሰጡ ኮርሶች ናቸው እናም አብዛኛውን ጊዜ ገንዘብ ያስከፍላሉ.

## የመንግስት / የግል ትምህርት ቤት

የሕዝብ/ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ነፃ ናቸው። ወንዶች እና ሴቶች ልጆች አንድ ላይ ትምህርት ይማራሉ። ትምህርቶቹ ከእምነት ገለልተኛ ናቸው።. አብዛኛዎቹ ልጆች እና ወጣቶች (95 ከመቶ) የሚሆኑት ለግዴታ ትምህርት ወደ የሕዝብ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። የግል ትምህርት ቤቶችም አሉ። ልጅዎን ወደ የግል ትምህርት ቤት ከላኩ፣ ለትምህርት ቤቱ በግልዎ መክፈል አለብዎት።.

## የወላጆች መብት እና ግዴታዎች

ልጅዎ በትምህርት ቤት ምን እየሰራ እንደሆነ እና በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ያህል አቋም ላይ እንዳለ ትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለበት። ለዚህም ነው ከእርስዎ እና ከመምህሩ ጋር ውይይቶች ያሉት።. በተጨማሪም መምህራን በትምህርት ቤት ልጅዎ ባለበት ክፍል ውስጥ ላሉ ወላጆች ሁሉ የሚያሳውቁባቸው የወላጆች ምሽቶችም አሉ። እና ስለ ትምህርት ቤቱ መረጃ ያላቸው ዝግጅቶች አሉ።. በእነዚህ ንግግሮች እና ዝግጅቶች ላይ መገኘት አለቦት። ልጅዎ በመደበኛነት ትምህርት ቤት እንዲከታተል የማረጋገጥ ሃላፊነት አለብዎት። ምናልባት ልጅዎ ለንድ ጊዜ ትምህርት ቤት መሄድ አይችል ይሆናል፣ ለምሳሌ ታሞ ከሆነ።. ይህ ከሆነ ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለብዎት።. እንዲሁም ልጅዎ የቤት ስራውን መስራቱን ማረጋገጥ አለብዎት። በዚህ ልጅዎን መደገፍ ይችላሉ።. ለምሳሌ በትምህርት ቤት ምን እየሰራ እንደሆነ መጠየቅ ይችላሉ። እና የቤት ስራውን በመደበኛነት መመልከት ይችላሉ።በዚህም ፍላጎት እንዳለዎት ያሳያሉ።
ስለ ስዊዘርላንድ የትምህርት ስርዓት ጥሩ አድርገው ካላወቁ፣ በዝግጅቶች ላይ የበለጠ ማወቅ ይችላሉ። በተለይ ለስዊዘርላንድ አዲስ ለሆኑ ሰዎች የመረጃ ዝግጅቶች አሉ። ስለዚህ ዝግጅቶቹ ብዙውን ጊዜ በጀርመን ሳይሆን በሌሎች ቋንቋዎች ነው።.

## ጥያቄዎች / እገዛ

ስለ ትምህርት ቤቱ ጥያቄ ካለዎት ሁል ጊዜ መምህሩን ማነጋገር አለብዎት። ድጋፍ ከፈለጉ መምህሩ ለእርስዎም ዝግጁ ነው። መምህሩ ምናልባት ልጅዎ የሆነ ነገር እንደሚያስፈልገው ሊሰማው ይችላል፣ ወይም መምህሩ ስለ ልጅዎ ጥያቄ ሊኖረው ይችላል።. ከዚያም መጀመሪያ ከርስዎ ጋር ይነጋገራል። ወላጆች እና አስተማሪዎች አብረው በደንብ ተጋግዘው ቢሰሩ በጣም ጠቃሚ ነው። ምናልባት ልጅዎ የአእምሮ ወይም የማህበራዊ ችግር ሊኖረው ይችላል።. የትምህርት ቤቱ ሳይኮሎጂካል አገልግሎት (Schulpsychologischer Dienst) እርስዎን እና ልጅዎን ይረዳል። እርዳታው ነፃ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/schule-und-bildung/obligatorische-schule

# የሙያ ትምህርት / መካከለኛ ትምህርት ቤት

ከግዴታ ትምህርት ቤት በኋላ አብዛኞቹ ወጣቶች የሙያ ስልጠና ይቀጥላሉ። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለመማር ከፈለጉ፣ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ያስፈልግዎታል።. በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባካሎሬት መውሰድ ይችላሉ። በሙያ ስልጠናዎ ወቅት ባካሎሬት መውሰድ ይችላሉ።

## የትምህርት አስፈላጊነት

ጥሩ ትምህርት እና ጥሩ ስራ በስዊዘርላንድ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ካገኘህ፣ በኋላ ላይ ብዙ የስራ እድሎች ይኖርሃል። ከግዴታ ትምህርት ቤት በኋላ ለሙያዊ ህይወትዎ (Sekundarstufe II). ለማዘጋጀት የተለያዩ አማራጮች አለዎት። ከተጨማሪ ስልጠና ጋር፣ ጥሩ ስራ ለማግኘት ቀላል ይሆንልዎታል።
ስለ ስልጠና እና ስለ ተጨማሪ ትምህርት ጥያቄዎች አሉዎት? የስራ፣ የጥናት እና የሙያ ምክር አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ወጣቶችን እና ወላጆችን ይመክራል። የምክር አገልግሎቱ ነፃ ነው።

## መሰረታዊ የሙያ ትምህርት

ከግዴታ ትምህርት በኋላ፣ አብዛኞቹ ወጣቶች መሰረታዊ የሙያ ስልጠናዎችን (የሙያ ልምምድ፣ Berufslehre). ያደርጋሉ። በሙያ ልምምድ ጊዜ በአንድ ኩባንያ ውስጥ ይሰራሉ። እዚያም ለስራዎ የሚያስፈልጉዎትን ተግባራዊ ክህሎቶች ይማራሉ።. በተጓዳኝ ወደ ሙያ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ።. ከ250 ለሚበልጡ ሙያዎች የልምምድ ትምህርት ማድረግ ትችላለህ። ትምህርቱ በ 2 እና 4 ዓመታት መካከል ይወስዳል። በመጨረሻዎቹ ሁለት የትምህርት አመታት እራስዎ የስራ ልምድየሚያደአርጉበት ድርጅት መፈለግ አለብዎት። ትምህርት ቤቱ በዚህ ረገድ ይረዳዎታል።. ብኖም ግን ወላጆችዎም መርዳት አለባቸው። የስራ፣ የጥናት እና የሙያ የምክር አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ለወጣቶች የተለያዩ አቅርቦቶች እና ምክሮች አሏቸው። የምክር አገልግሎቱ ነፃ ነው። እንዲሁም በሚለማመዱበት ወቅት ወይም በኋላ የሙያ ባካሎሬት (Berufsmaturität) ማድረግ ይችላሉ። ይህ በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ለመማር ያስችልዎታል።.

## መካከለኛ ትምህርት ቤቶች

መካከለኛ ትምህርት ቤቶች (Mittelschulen) ለዩኒቨርሲቲ ወይም ለተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ (Fachhochschule) ለቀጣይ ትምህርት ያዘጋጅዎታል። ተማሪዎቹ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ሰፊ አጠቃላይ ትምህርት ያገኛሉ።
የተለያዩ መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፣

- መካከለኛ ትምህርት ቤቶች ከሁለተኛ ደረጃ ባካሎሬት ጋር፡ ከዚያም በመቀጠል በዩኒቨርሲቲ መማር ይችላሉ። ነገር ግን በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም መማር ይችላሉ።
- ከመካከለኛ ትምህርት ቤቶች ልዩ ባለሙያ ወይም የሙያ ባካሎሬት ያላቸው፣። ከዚያ በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ መማር ይችላሉ። ምናልባት በዩኒቨርሲቲ ውስጥም መማር ይችላሉ።. ለዚህ ግን ፈተና ማለፍ አለብዎት። አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ።

## አሸጋጋሪ አቅርቦቶች

ዕድሜዎ ከ18 እስከ 25 አመት ነው እና የግዴታ ትምህርትን ከጨረሱ በኋላ ወደ ባዝል-ከተማ ካንቶን አዲስ ተዛውረዋል። ምናልባትም ከማእከሉ አቅርቦቶች፣ በአሸጋጋሪ አቅርቦቶች (Brückenangebote፣ ZBA) በሚቀርበው አቅርቦት ላይ መሳተፍ ይችሉ ይሆናል። ሁሉም በስራ ህይወትዎ ውስጥ አዲስ ጥሩ ጅምር እንዲሆኖት ነው።. አሸጋጋሪ አቅርቦት ተለማማጅነት ወይም ልምምድ ለማግኘት ይረዳዎታል። ፍላጎት አለዎት? ካለዎት በአሸጋጋሪ አቅርቦቶች ማእከልን ያነጋግሩ (Zentrum für Brückenangebote)።.

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/schule-und-bildung/berufsbildung--mittelschulen

# ዩንቨርስቲ / ተግባራዊ የሳይንስ ዩንቨርስቲ

በስዊዘርላንድ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዩኒቨርሲቲዎች አሉ። ዩኒቨርሲቲዎች እና ተግባራዊ የሳይንስ ዩንቨርስቲ ናቸው።በውጭ አገር የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማዎች ለመግባት፣ ዩኒቨርሲቲውን ጋር በቀጥታ መጠየቅ አለብዎት።.

## የዩንቨርስቲ የትምህርት ስርዓት

የስዊዘርላንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዩኒቨርሲቲዎች እና በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች (Fachhochschulen) የተከፋፈሉ ናቸው። በተግባራዊ ሳይንስ ዩኒቨርስቲዎች ትምህርቱ በተግባር ላይ ያተኮረ ሲሆን በዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በቲዎሪ ላይ ያተኮረ ነው። ሁለቱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአውሮፓ ቦሎኛ ስርዓት መሰረት እኩል እና የተደራጁ ናቸው።. የተጠናቀቁት በባችለር ወይም በማስተርስ ዲግሪ ያስመርቃሉ፣ ይህም በመላው አውሮፓ ዕውቅና አለው።

## የመግቢያ ፍቃድ

እንደ የዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የመግቢያ መስፈርቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ። በስዊዘርላንድ በሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማዎች ዩኒቨርሲቲዎች መግባት የተረጋገጠ ነው። የውጭ አገር ሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማዎች በእርግጠኝነት ዕውቅና አያገኙም። ለትምህርት ኮርስ ለመግባት፣ መማር የሚፈልጉትን ዩኒቨርሲቲ (ዩኒቨርስቲ/ተግባራዊ የሳይንስ ዩኒቨርስቲ) በቀጥታ ማነጋገር አለብዎት። በአጠቃላይ በጣም ጥሩ የጀርመንኛ እውቀት መስፈርት ነው።. ልዩ አቅርቦት ያላቸው አሉ፣ አንዳንድ ኮርሶች ሙሉ በሙሉ በእንግሊዝኛ ይቀርባሉ። የስራ፣ የጥናት እና የሙያ የምክር አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ስለ ሶስቱም የትምህርት ደረጃዎች ከተለያዩ አማራጮች ጋር ነፃ መረጃ ይሰጣል።

## ከፍተኛ የሙያ ትምህርት

ከዩኒቨርሲቲዎች በተጨማሪ በከፍተኛ የሙያ ስልጠና በስዊዘርላንድ ውስጥ ትምህርት ለመቀጠል ተወዳጅ አማራጭ ነው። ባለሙያዎች እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ እና እንዲያበለጽጉ እንዲሁም የአስተዳደር የሃላፊነት ስራዎችን መስራት እንዲችሉ ያስችላቸዋል።. ከፍተኛ የሙያ ስልጠና ከመሠረታዊ የሙያ ስልጠና (የሙያ ልምምድ፣ Berufslehre) በኋላ ይከተላል።. ለዚህ ምንም የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ አያስፈልግም። .የስራ፣ የጥናት እና የሙያ ምክር አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ስለ ተለያዩ አማራጮች ነፃ መረጃ ይሰጣል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/schule-und-bildung/universitaeten--fachhochschulen

# የዲፕሎማ ዕውቅና

**የውጭ ዲፕሎማዎች እና ዲግሪዎች በስዊዘርላንድ ውስጥ ሁልጊዜ ተቀባይነት አያገኙም። በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን ዲፕሎማው እውቅና ማግኘት ይቻላል።. ይህም ለአንዳንድ ሙያዎች ግዴታ ነው።.**

## ዕውቅና

የውጭ አገር ዲፕሎማ ያላቸው ሰዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች በስዊዘርላንድ ውስጥ እውቅና ሊያገኙ ይችላሉ።. የሚሰጠው እውቅናው የውጭ አገር ዲፕሎማው ወይም ዲግሪው ከስዊዘርላንድ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ጋር እኩል መሆኑን ያረጋግጣል። ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሙያዎች (ለምሳሌ የነርሲንግ ባለሙያዎች፣ መምህራን፣ ወዘተ) ከሆነ ሙያውን ለመለማመድ እውቅና ማግኘት ያስፈልጋል። በሙያው ወይም በስልጠናው ላይ በመመስረት፣ የተለያዩ አካላት እውቅና የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው።. እውቅናን ለማግኘት ክፍያ ያስከፍላል።. ከብሔራዊ የመገናኛ ማዕከል ለዲፕሎማ እውቅና ወይም ከስራ ጥናት እና የሙያ ምክር አገልግሎት ማዕከል (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) መረጃ ማግኘት ይቻላል።

## የደረጃ ማረጋገጥ

ቁጥጥር በማይደረግባቸው ሙያዎች ጋር በተያያዘ በስዊዘርላንድ ውስጥ ለመስራት የዲፕሎማ ወይም የብቃት ማረጋገጫ እውቅና አያስፈልግም። ለእነዚህ ሙያዎች የደረጃ ማረጋገጫ (Niveaubestätigung) ማመልከት ይቻላል። ይህ የሚያሳየው የውጭ አገር ዲፕሎማ የስዊዘርላንድ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ነው። ሥራ ሲፈልጉ ማረጋገጫው ሊረዳዎት ይችላል። የደረጃ ማረጋገጫ መረጃ ከብሔራዊ የመገናኛ ማዕከል ለዲፕሎማ ዕውቅና (Nationale Kontaktstelle für Diplomanerkennung) ወይም ከስራ፣ ጥናቶች እና የሙያ ምክር አገልግሎት ማዕከል (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) ማግኘት ይቻላል።

## የሙያዊ ብቃትን በኋላ ማሟላት

ሙያዊ ልምድ ያላቸው አዋቂዎች ነገር ግን እውቅና ያለው ዲፕሎማ ወይም እውቅና ያለው ብቃት የሌላቸው፣ መሰረታዊ የሙያ ስልጠና ወይም ከፍተኛ የሙያ ስልጠና የስዊስ መመዘኛዎችን ከጊዜ በኋላ ማሟላት ይችላሉ። የአሰራር ሂደቱ በቀድሞው ትምህርት፣ በሙያዊ ልምድ እና በእድሜ ላይ የተመሰረተ ነው። ያም ሆነ ይህ ጥሩ የጀርመንኛ እውቀት ዋነኛ መስፈርት ነው (ደረጃ B1/B2 በGER መሠረት) ። ፍላጎት ያለው ሰው ከሙያ፣ ጥናት እና የስራ አማካሪ አገልግሎት (Berufs-, Studien- und Laufbahnberatung) በነጻ መረጃ እና ምክር ማግኘት ይችላል። የሙያ ብቃትን ከጊዜ በኋላ ያሟላ ማንኛውም ሰው፣ በስራ ገበያው ላይ ያለውን እድል ያሻሽላል እናም ተጨማሪ ስልጠና የማግኘት እድል ይኖረዋል።.

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/schule-und-bildung/diplomanerkennung